# ከውሃ መስኖ፣ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድ ላይ የተሰጠ ግብረ- መልስ

## 1. መግቢያ፡-

በህዝብ ተወካዮች ም/ቤት የውሃ መስኖ፣ቆላማ አካባቢ እና አካባቢ ልማት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሚቴ ከተሰጡት ተግባርና ኃላፊነቶች አንዱ የአካባቢ ጥበቃ ባለስልጣን ዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ሂደትና ትግበራን መከታተል መደገፍና መቆጣጠር ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ቋሚ ኮሚቴያችን የኮሚሽኑን የ2014 በጀት ዓመት ዕቅድን በመገምገም የሚከተለውን ግብረ-መልሰ ሰጥቷል፡፡

## 2. በጥንካሬ የታዩ፡-

- የተገልጋይ እርካታን ለማሰደግ በተቀመጠው ስታንዳርድ መሰረት ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት በመስጠት የተገልጋይ እርካታ ከ 83 % ወደ 88% ለማሳደግ መታቀዱ፤
- ከባለስልጣኑ ተግባርና ሀላፊነት አንጻር ቅንጅታዊ አሰራር ወሳኝ በመሆኑ ከዘርፉ መ/ቤቶች፣ ከክልሎችና ከከተማ አስተዳደሮች ጋር በጋራና በመደጋገፍ ለመስራት መታቀዱ፣
- የሀብት ግኝትን ማሳደግን ከአጋር ሀገሮች እና ድርጅቶች 50 ሚሊዮን ዶላር ለማሰባሰብ በዕቅድ መያዙ፤
- ለአየር ንብረት ለውጥ የማይበገር የአረንጓዴ ኢኮኖሚ ትግበራን ውጤታማነት ለማሻሻል 144.99 MtCO2eq የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት መጠን ለመቀነስ መታቀዱ፤
- የአካባቢ ህግ ተከባሪነት ለማጎልበት 6 የአካባቢ ህግ ስርዓቶችን ለማዘጋጀት መታቀዱ፤
- አገራዊ የደን ሽፋንን ለማሳደግ 325 ቶን የዛፍ ዘር በማሰብሰብና በማሰራጨት 4 ቢሊዮን የደን ችግኞችን ለማፍላት መታቀዱ፤
- ባለስልጣኑ የተጠሪ ተቋማትን ዋና ዋና ተግባራት የዕቅድ አካል በማድረግ ማሳየት መቻሉ፣

- የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ሥርዓትን መሠረት በማድረግ ለ7300 የልማት ፕሮጀክቶች የይሁንታ ፈቃድ (የግንባታ ፈቃድ) እንዲያገኙና እንዲተገበሩ እንዲሁም ለ1520 ነባር ፕሮጀክቶች የአካባቢና ማህበረሰብ አያያዝ ዕቅድ እዲያቀርቡና እንዲያጸድቁ ለማድረግ መታቀዱ፣
- የወጣቶችና ሴቶች ተሳታፊነትና ተጠቃሚነትን ለማሳደግ በደን ዘርፍ በሚፈጠርላቸው የሥራ ዕድል ወጣቶችና ሴቶች በቁጥር ለይቶ ማቀድ መቻሉ፣
- የክትትልና ድጋፍ ስርዓት በዕቅዱ ውሰጥ የተዘረጋ መሆኑ፣

## 3. ቀጣይ በዕቅዱ ውስጥ ሊካተቱ የሚገባቸው ጉዳዩች፡-

- የ2014 በጀት ዓመት እቅድ ውስጥ ቁልፍ ችግሩን እና የመፍትሄ እርምጀዎች ለይቶ ያልተቀመጣ ስለሆና እንድቀመጥ ማድረግ፣
- የኦዲት ግኝትን በተመለከታ በ2013 በጀት ዓመት ኦዲት ስለመደረጉ ቢያሳይም የኦዲት ግኝቶችን በግልፅ ያልተቀመጠ መሆኑ፣
- የመረጃ ቴክኖሎጂ አቅርቦትና ሽግግርን ለማሳደግና የዘርፉን የመረጃ አሰባሰብ አያያዝና አጠቃቀም ለማሻሻል አሁን ካለበት ከ20 መቶ 30 ከመቶ ለማሳደግ መታቀዱ የለንበት የቴክኖሎጂ ዘመን የለገነዘበ በመሆኑ ትኩረት ተሰጥቶበት መታቀድ አለነት
- ባለስልጣኑ የኪራይ ሰብሳቢነት፣ የመልካም አስተዳደር እና የስነ-ምግባር ችግሮችን ለመፍታት ችግሮቹን በመለየትና መፍትሄዎችንም በመካተት የዕቅዱ አካል ማድረግ አለበት፤
- ባለስልጣኑም ሆነ በተጠሪ ተቋማት ላይ በፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት የታዩ የክዋኔም ሆነ የፋይናንስ የኦዲት ግኝቶች ላይ ለማስተካከል የሚሠሩ ሥራዎችና የሚወሰዱ የእርምት እርምጃዎት በእቅዱ መካተት አለባቸው፤
- ባለስልጣኑ በበጀት ዓመቱ ዕቅድ አፈፃፀም ወቅት ሊያጋጥሙ የሚችሉ ችግሮችና መፍትሔዎችን በዝርዝር በማስቀመጥ የዕቅድ አካል ማድረግ አለበት፣
- የዘርፈ-ብዙ ጉዳዮች በተሟላ መልኩ የዕቅድ አካል ተደርገው ያልታቀዱ በመሆኑ በቀጣይ ተካቶ መታቀድ አለበት

ለአብነት፡-

- ኤች አይቪ ኤድስ ፣ የአካል ጉዳተኞችን እንዲሁም ኮቪድ 19 ጉዳይም በዝርዝር ተብራርቶ መታቀድ አለበት፡፡

- ባለስልጣኑ ከባለድረሻ አካላት ጋር እንዴት እንደሚሰራና ባለድርሻ አካላቶችን በአግባቡ ለይቶ በዕቅድ ውስጥ መካተት ይኖርበታል፣

## 4. ማጠቃለያ፡-

ቋሚ ኮሚቴው የኮሚሽኑን የ2014 ዕቅድ በዝርዝር የገመገመ ሲሆን በቀጣይ በዕቅድ ሊካተቱና ሊስተካከሉ የሚገባቸውን ጉዳዩች በማካተትና በማስተካከል እንዲላክልን እያሳሰብን ቋሚ ኮሚቴያችን የክትትልና ቁጥጥር ስራውን አጠናክሮ የሚቀጥል መሆኑን እንገልፃለን ፡፡